## ው ሣ ኔ

1. የፈንታሌ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 1/89 ጥር 1 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ብይን የዞን 3 ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 0449 መጋቢት 10 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ በፍ.ብ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች መ/ቤት እንዲቀጠር በፍርድ ውሣኔ ያላገኘ ስለሆነ ሥራ ላይ ላልነበረበት ጊዜ የደመወዝ ስኬል ሊጠበቅለትም ሆነ ደመወዝ ሊከፈለው አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



የሰ/መ/ቁ. 30956

ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን እቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

መድኀን ኪሮስ

አመልካች፡- የወረዳ 5 አጠቃላይ ነጋዴዎች ማኀበር ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ በድሉ ጫላ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በጉዳዩ ላይ ክርክር የተጀረመው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ የሥር ከሣሽ ሰኔ 9 ቀን 1996 ዓ.ም. አዘጋጅተው ባቀረበው የክስ ማመልከቻ ከጥቅምት 19 ቀን 1992 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ግንቦት 30 ቅን 96 ዓ.ም. በማኀበሩ በጥበቃ አባልነትና በጥበቃ ቡድን መሪነት በወር ብር 250 ደመወዝ እየተከፈለኝ ሳገለግል የቆየሁ ሲሆን ድርጅቱ ግንቦት 30 ቀን 1996 ዓ.ም. ያለ አንዳች ጥፋትና ማስጠንቀቂያ ከሥራ በቃል አሰናብቶኛል፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የስንብት፣ የካሣ፣ የማስጠንቀቂያ፣ የዓመት ዕረፍት ክፍያ እንዲሁም የሥራ ልምድ ማስረጃ እንዲሰጠኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

ተከሣሽ ማኀበርም ሐምሌ 7 ቀን 1996 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው መልስ ከሣሽ ከሥራ በተደጋጋሚ ስለሚቀሩ፣ ትዕዛዝ ስለማያከብሩ፣ የተመደቡበትን የጥበቃ ቦታ ለቀው ስለሚሄዱ፣ በስራ ላይ አምባጓሮ ስላነሱ እና የሥራ ሰዓት ስለማይቀበሉ በአዋጁ አንቀጽ 27/1/ሀ/ መሠረት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶቸው በአግባቡ የተሰናበቱ በመሆኑና ደመወዛቸውም ብር 200 እንጂ ብር 250 ባለመሆኑ ክሳቸው ተቀባይነት የለውም ተብሎ እንዲወስንልን በማለት ተክራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ካዳመጠ በኋላ ከሣሽ የተሰናበቱት በፈፀሙት ጥፋት መሠረት ስለመሆኑ በማስረጃ በመረጋገጡ የጠየቁት ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም ያልወሰዱት የዓመት ዕረፍት ክፍያ ግን በደመወዛቸው መሠረት እንዲከፈላቸው የሥራ የምስክር ወረቀትም እንዲሰጣቸው ሲል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ ተመልክቶ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የአሁኑ ተጠሪ የሥር ከሣሽ ከሥራ የተሰናበቱት በሕገወጥ መንገድ በመሆኑ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዛቸው እንዲከፈላቸው ወደ ሥራም እንዲመለሱ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች የሥር ተከሣሽ ያቀረበው የሰበር አቤቱታም የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ቅሬታውም ተጠሪው ከስራ የተሰናበቱት ለክሱ በሰጠነው መልስ በጠቀስናቸው ጥፋቶች ምክንያት መሆኑን አስረድተን እያለ የከፍተኛው ፍ/ቤት ስንብቱ ሕገወጥ ነው፣ ተጠሪው ወደ ሥራ ይመለሱ፣ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝም ይከፈላቸው በማለት የሰጠው ውሣኔ ማስረጃችንን ያላገናዘበና ተጠሪው ካቀረቡት ክስ እና ዳኝነት ከጠየቁበት ጥያቄ ውጭ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ በመሆኑም የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሮ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ እንዲፀና እንዲወስንልን የሚል ነው፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር ሰሚ ችሎትም ተጠሪው ወደ ሥራ ለመመለስ ክስ ሳያቀርቡ ፌ/ከ/ፍ/ቤት ስንብቱ ሕገወጥ ነው፣ ተጠሪው ወደ ሥራ ይመለሱ ብሎ የመወሰነው በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን መመርመር በማስፈለጉ አቤቱታው ያስቀርባል ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪው ደግሞ በሰጡት መልስ የተሰናበትኩት ያለ አንዳች ጥፋትና ያለማስጠንቀቂያ ስለመሆኑ በማስረጃዬ ያረጋገጥኩኝ በመሆኑ የፌ/ከ/ፍ/ቤት ስንብቱ ሕገወጥ ነው፣ ሠራተኛው ወደ ሥራው መመለስ አለበት፣ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝም ሊከፈለው ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ የተሰጠ እንጂ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት አይደለም፡፡ እንዲያውም



ውሣኔው ተሻሽሎ የዓመት ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለኝ ሊወሰንልኝ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም የመልስ መልሱን በማቅረብ ከመዝገቡ ጋር አያይዟል፡፡

በበኩላችን ደግሞ አመልካች ተጠሪውን ያሰናበታቸው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የፌ/ከ/ፍ/ቤት ተጠሪው ወደ ሥራ ሊመለሱ፣ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዛቸውም ሊከፈላቸው ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ በቀረበው ክስ ዳኝነት የተጠየቀበትን ነጥብ መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች መሠረት በማድረግ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ተጠሪው ሰኔ 9 ቀን 1996 ዓ.ም. አዘጋጅተው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ማኅበሩ ከስራ ያሰናበተኝ በሕገወጥ መንገድ ነው ቢሉም ማኀደራቸው ሲታይ በተለያየ ጊዜ ከስራ በመቅረት፣ የተመደቡበትን የጥበቃ ቦታ ለቆ በመሄድ እና የሥራ ሰዓትን ባለማክበር የተገመገሙና ይህን ጥፋት የፈፀሙ ስለመሆናቸው የሥር ፍ/ቤቶች መዝገቦች ስለሚያስረዱና እነዚህ ጥፋቶች ደግሞ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብቱ እንደሚችሉ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 የተደነገገ በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ደግሞ ተጠሪው ባቀረቡት ክስ ዳኝነት የጠየቁባቸው ነጥቦች የስንብት፣ የካሣ፣ እና የዓመት ዕረፍት ክፍያዎችንና የሥራ ልምድ ሰርተፊኬት ማግኘትን የተመለከቱ እንጂ ውዝፍ የወር ደመወዝ ክፍያና ወደ ሥራ የመመለስ ጥያቄን ያካተቱ አይደሉም፡፡ ስለሆነም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ተጠሪው የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎአቸው ወደ ሥራ እንዲመለሱ በማለት የወሰነው አግባቡ ባለመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡